# ፊደል እንደገና

ባዬ ይማምና ቲም '89*

## 1. መግቢያ

ይህ ፅሁፍ የተዘጋጀው በጋራ ነው:: ተጋሪዎቹ የዚህ የ1989 ዓ.ም. TEAM 503 ተማሪዎችና የዚሁ ትምህርት መምህር ናቸው:: ትምህርቱ የአማርኛን ድምፆችና ፎኒሞች፣ የፎኒሞቹን አቀነጃጀትና በየቅንጅቱ ላይ የሚካሄዱትን ድምፀ-ልሳናዊ ሂደቶች የሚመለከት ነው:: ይህ የትምህርቱ ስነ-ልሳናዊ ዘርፍ ነው:: ሌላው ዘርፍ ትምህርቱ ለአማርኛ ቁዋንቁዋ ትምህርት ያለው አግባብነት ነው:: በዚህ በኩል የቁዋንቁዋውን ስርዓተ-ፅህፈት፣ የዚሁ መሳሪያ የሆነውን ፊደልና የእሱኑ ትምህርት ከቁዋንቁዋው ፎኒሞች ጋር እያገናዘቡ ማየት ትልቁ ስራ ነበር:: ከስራው በተለይ ስርዓተ-ፅህፈቱን የሚመለከተው ክፍል በአማርኛ ላይ ያተኩር እንጅ አጠቃላይ ዕይታው ቢያንስ የሴምና የኩሽ ቁዋንቁዎቹንም የሚያካትት ነበር:: ስርዓተ-ፅህፈቱ አስፈላጊው ማስተካከያ እየተደረገለት ከአማርኛና ከሌሎች የሴም ቁዋንቁዋዎች አልፎ ለማንኛውም የሀገራችን ቋንቋ ሊያገለግል እንደሚችል ከዚህ በፊትም የተገለጸ ጉዳይ ነበር (ባዬ 1984):: አሁን ደግሞ ጉዳዩ ከሀሳብ ተራ አልፎ በተግባር ወደሚውልበት ደረጃ ደርሶአል:: ይህም ፊደሉ እጅግ በጣም ትንሽ ማስተካከያ ተደርጎለት አሉ የሚባሉትን የአማርኛ ስርዓተ-ፅህፈታዊ ችግሮች ከማስወገድ አልፎ ኩሻዊ ለሆኑ አንዳንድ ቁንቁዋዎችም መፃፊያ ሊሆን መብቃቱ ነው:: የተደረገው ማስተካከያና የዚሁ መሰረት የሆኑት ዝርዝር ስርዓተ-ፅህፈታዊና ስነ-ልሳናዊ ጉዳዮች የፅሁፉ አቢይ ይዘቶች ናቸው::

---

* ምርምሩ በጋራ ከተሠራ በሁዋላ ጥንቅሩና ጽሑፉ በትምህርቱ መምህር የተዘጋጀ መሆኑን እንገልጻለን::

## 2. የአማርኛ ፎኒሞች

አማርኛ 27 ተናባቢና 7 አናባቢ በጠቅላላው 34 ፎኒሞች አሉት፡፡ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው:-

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተናባቢ:- | ብ | ም | ው | ፍ | ጥ | ት | ስ | ድ | ዝ |
| | ል | ር | ን | ሽ | ጅ | ዥ | ች | ኝ | ጭ |
| | ይ | ክ | ግ | ቅ | ህ | ክ$^{ው}$ | ግ$^{ው}$ | ቅ$^{ው}$ | ህ$^{ው}$ |
| አናባቢ:- | እ | አ[1] | ኣ | ኢ | ኤ | ኡ | ኦ | | |

እነዚህ ነባር ፎኒሞች ናቸው፡፡ ከነዚህ በተጨማሪ ከሌሎች ቋንቋዎች በመጡ ቃላት አማካይነት የገቡ አራት ተናባቢ ፎኒሞች አሉ፡፡ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡፡

| | |
|---|---|
| ጵ | (ከግሪክ) |
| ፕ | (ከእንግሊዝኛ) |
| ፅ/ጽ | (ከግዕዝ) |
| ዕ | (ከግዕዝ) |

እነዚህ እንደ ነባሮቹ ፎኒሞች በየቃሉ ሳይሆን በተወሰኑ ባዕድ ቃላት ውስጥ ብቻ ስለሚገኙ ስርጭታቸው ውሱን ነው፡፡ መደበኛ በሚባለው የከተማ አማርኛ እንጅ ምንም የውጭ ቋንቋ በማይችሉ ተወላጅ የገጠር አማርኛ ተናጋሪዎች ንግግር ውስጥ አይገኙም፡፡ ቢገኙም ከላይ በሚታዩበት ቅርፅ ሳይሆን ለነሱ የሚቀርበውን ተወላጅ የአማርኛ ድምፅ መስለው ነው፡፡ ይህም እንደሚከተለው ሲሆን ነው፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ምሳሌ | ፖሊስ | ፑ/ቡሊስ |
| | ጳጳስ | ባባስ |
| | ጠረጴዛ | ጠረቤዛ |
| | ፀበል | ጠበል |
| | አዕምሮ | አይምሮ |

[1] ይህ አናባቢ (አ) በተለመደው አፃፃፍ የሚወከለው በ[ኧ] ነው፡፡ ይሁን እንጅ የሚነበበው እንደ ራብዑ [ኣ] ነው፡፡ በዚሁ ፅሁፍ [ኧ] በሱ ፈንታ [አ] 'ን እንጠቀማለን፡፡ ስለዚህ እንደ አወቀ ያሉ በ [አ] የሚጀምሩ ቃላት ኣወቀ ተብለው በራብዑ [ኣ] ተፅፈዋል፡፡

እነዚህና ተወላጅ የሆኑት ተናባቢ ፎኒሞች ባንድ ላይ 31 ይሆናሉ፣ ከሰባቱ አናባቢዎች ጋር ጠቅላላ የፎኒሞቹ ቁጥር 38 ይሆናል። እነዚህ 38 ፎኒሞች 'የመደበኛው'፥ ማለትም የቅይጡ አማርኛ ፎኒሞች ናቸው። የገጠሩ አማርኛ ፎኒሞች ቀደም ሲል የተጠቀሱት 27 ተናባቢዎችና ሰባቱ አናባቢዎች ብቻ ናቸው።

በመሠረቱ በነዚህ በ34ቱ ፎኒሞች ብቻ መጠቀም ይቻል ነበር። አሁንም ይቻላል። ግን ቋንቋዋ መግባቢያ ብቻ ሳይሆን መታወቂያም በመሆኑ ትምህርት ቀመስ የሆነው ክፍል ቀመስነቱን ለማሳወቅ ሲል ብቻ ከላይ እንደ ተጠቀሱት ያሉ የውጭ ቃላትን መጠቀም የግድ ሆኖበታል። ትምህርት የቀመሰው ብቻ ሳይሆን የሸተተውም ቢሆን ዛሬ ለቅይጡ አማርኛ ያለው በጎነት በጣም ግልፅ ነው። በዚህ ክፍል ለሚመደቡ የቋንቋው ተጠቃሚዎች፡-

ጠበል ጣዲቅ ሊቀምሱ የመጡትን ሰዎች
ፎሊሱ በጠራራ ጠሀይ ሲያንቃቃቸው ዋለ።

የሚል ሰው ማህበራዊ ምድቡ 'እንደበቱ የጎለደፈ፥ ልብሱ ያደፈ' ከሚባለው መሀይም ባላገር ጋር ነው (ባዬ፡ 1976)። ይህ የቋዋንቋዋው ማህበራዊነት የሚንፀባረቅበት ጉዳይ ነው። ስለሆነም እሱን ትተን ስነ-ልሳናዊ ባህሪው ወደሆነው ወደ ፎኒሞቹ እንመለስና ከስርዓተ-ፅህፈቱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንመልከት።

## 3 ስርዓተ-ፅህፈቱ

ተደጋግሞ ሲነገር የምንሰማው የግዕዙ ስርዓተ-ፅህፈት ቀለማዊ መሆኑን ነው፣ (Bender:1976፤ Cowley: 1967፤ Cohen: 1970፤ Mullen: 1986፤ ባዬ፡ 1984)። ከነዚህ ሁሉ የሚለየው ታደሰ (1994) ነው። ታደሰ ስርዓተ-ፅህፈቱ ቀለማዊ አለመሆኑን ቀለማዊ ቆቸው ከሚባሉት እንደቾሮኪ ካሉ ቋንቋዎች ስርዓተ-ፅህፈት ጋር በማነፃፀር አሳይቶአል። እንደ ቾሮኪ ባሉ ቀለማዊ ስርዓተ-ፅህፈቶች እያንዳንዱ ምልክት የሁለት ተናባቢና የአንድ አናባቢ ቅንጅት የሆነ ቀለምን ይወክላል። ቀለሞቹን በሚወክሉት ምልክቶች መካከልም የቅርፅ ተመሳሳይነት የለም። ለምሳሌ የሚከተሉትን የቾሮኪ ቀለሞችናምልክቶቻቸውን እንመልከት፡-

dla dle dli dlo dlu dlʌ (Crystal, 1987:201)

የቀለሞቹ ቅደም ተከተል፡

ድላ ድሌ ድሊ ድሎ ድሉ ድለ

የሚል ነው። ከአማርኛው 'ደ ዱ ዲ ዳ ዴ ዶ' ጋር የሚመሳሰል አካሄድ ያለው ይመስላል። ይምሰል እንጅ እያንዳንዱ የቾሮኪ ምልክት ከሌላው ጋር ምንም አይነት የቅርፅ ተመሳሳይነት የለውም። በአማርኛው አቻ ምልክቶች መካከል ግን ጉልህ የሆነ የቅርፅ ተመሳሳይነት አለ። የቾሮኪን ምልክቶች የሚማር ሰው እያንዳንዱን ምልክት ከሌላው ጋር እያገናዘበ ይለያል፤ ለምሳሌ ካዕቡን ከግዕዙ፥ ሳልሱን ከካዕቡ፥ ሃምሱን ከሳልሱ፥ ወዘተ እያስተያየ አንድዋን ከሌላዋ መለየት ይችላል። ይህ አይነቱ የቅርፅ ተመሳሳይነትና ከዚሁ ተመሳሳይነት ተነስቶ አንዱን ምልክት ከሌላው ጋር እያገናዘቡ መማር የቀለማዊ ስርዓተ-ዕህፈት ባህሪ ሊሆን አይችልም። ታደሰም ያለው ይህንን ነው። ይበል እንጅ ከዚህ አልፎ ስርዓተ-ዕህፈቱ ቀለማዊ ካልሆነ ምናዊ ነው? ወደሚል ጥያቄ አልሄደም።

ይህ ያሁኑ ዕሁፍ ከታደሰ ንዕዕራዊ ክርክር ተነስቶ የስርዓተ-ዕህፈቱን ምናዊነት ለመወሰንና ውሳኔውም በስርዓተ-ዕህፈቱ ልማዳዊ አጠቃቀምና በፊደል ትምህርት ላይ የሚያስከትለውን አንድምታ ለማየት ይሞክራል። ይህን ለማድረግ ግን ለረዥም ዘመን ሲወሳ የኖረውን የስርዓተ-ዕህፈቱን ቀለማዊነት እንደገና በጥንቃቄ መመርመር ተገቢ ይሆናል።

ስርዓተ-ዕህፈቱ ቀለማዊ ነው ሲባል የኖረበት ዋናው ምክንያት እያንዳንዱ ምልክት የአንድ ተናባቢና የአንድ ወይም የሁለት አናባቢ ድምጾችን ቅንጅት የሚወክል በመሆኑ ነው። ለምሳሌ 'በ' የሚለውን ግዕዛዊ ምልክት ብንመለከት ቁዋሚነቱ (ብ) ለሚለው ተናባቢና (አ፡ኧ)[2] ለሚለው አናባቢ ድምፅ ቅንጅት ነው። 'ቡ' የሚለው ደግሞ የ(ብ) እና የ(ኡ) ቅንጅት ምልክት ነው።

ይህ አይነቱ በተናባቢና በአናባቢ(ዎች) ቅንጅት ላይ የተመሠረተ ቀለማዊነት በከፊል ከስነ-ግጥም ጋር የተያያዘ ነው። በስነ-ግጥም ትምህርት እያንዳንዱ ስንኝ በሀረግ፥ እያንዳንዱ ሀረግ ደግሞ በቀለም እየተመጠነ ይጻፋል። በዚህ አይነት ምጣኔ ከሚለኩት የግጥም አይነቶች እጅግ የተለመደው የወል ግጥም


---

[2] /አ/ የሚለው አናባቢ <u>በስርዓተ-ዕህፈቱ</u> /ኣ/ ከሚለው አናባቢ አይለይም። በስርዓተ-ድምፅ ደረጃ ግን ሁለቱ የተለያዩ ድምፆችን የሚወክሉ የተለያዩ ምልክቶች ናቸው። ይህ ባይሆን ኖሮ /አ/ን በ/ኧ/፥ /ሀ/ን ደግሞ በ/ኸ/ ፋንታ መጠቀም እንችል ነበር። ይህም /ኧ/ን እና /ኸ/ን ከነዝርዝራቸው ስለሚያስወግድ የፊደሉን ቁጥር ይቀንስ ነበር። ያለምንም ወጪ።

የሚባለው ነው:: የዚህ አይነት ግጥም ሀረግ የስድስት ቀለሞች ቅንጅት ሲሆን ቀለሞቹ ደግሞ የተናባቢና የአናባቢ ቅንጅቶች ናቸው:: በየቅንጅቱ ውስጥ (እ) የሚባለው አናባቢ ብቻ ሊወድቅ ወይም ሊነሳ ይችላል::[3] ቀለሙ ከስድስት እንዳይበልጥ ሲፈለግ ይወድቃል (ይገደፋል)፤ ከስድስት እንዳያንስ ሲፈለግ ደግሞ ይነሳል:: ይህ አንዱ አይነት የቀለም ግንዛቤ ነው:: ከስርዓተ-ፅህፈቱ ጋር መጠነኛ ግንኙነት ያለውም ይኸው ነው::


ሌላው አይነት ቀለማዊነት ስነ-ልሳናዊ ነው:: ከስነ-ግጥሙም ሆነ ከስርዓተ-ፅህፈታዊው ቀለማዊነት በባህሪው የተለየ ነው:: ከሀረግ አመጣጠን ጋር ሳይሆን ቀደም ሲል ከተዘረዘሩት ከቁዋንቁዋው ፎኒሞች ስነ-ልሳናዊ የአቀነጃጀት ባህሪ ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው:: የስነ-ግጥሙም ሆነ የስርዓተ-ፅህፈቱ ቀለም የፎኒሞች ቅንጅት ከሚፈጥረው ቀለም ጋር አንድም ልዩም ሊሆን ይችላል:: ለዚህ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት:-

(ሀ) ሰው





3 ይህን ጉዳይ በተመለከተ Bender (1969)'ን ይመልከቱ::


(ለ) ሰርግ


ቀ
- አንድ ስነ-ልሳናዊ ቀለም
S ə r (ť)
- አንድ/ሁለት ስነ-ግጥማዊ ቀለም
ሰ ር ግ
- ሶስት ስርዓተ-ፅህፈታዊ ምልክቶች


(መ) ና


ቀ
- አንድ ስነ-ልሳናዊ ቀለም
n a
- አንድ ስነ-ግጥማዊ ቀለም
ና
- አንድ ስርዓተ-ፅህፈታዊ ምልክት

(ሰ) አፍ


ቀ
- አንድ ስነ ልሳናዊ ቀለም
a f((ť)
- አንድ/ሁለት ስነ-ግጥማዊ ቀለም
አ ፍ
- ሁለት ስርዓተ-ፅህፈታዊ ምልክት

(ረ) አልክ




ምልክቶች

ከምሳሌዎቹ የሚከተሉትን መገንዘብ ይቻላል፡፡

(ሀ) ከምሳሌ (መ) በስተቀር በሌሎቹ በሙሉ በስነ-ልሳናዊውም ሆነ በስነ-ግጥማዊው ቀለምና በስርዓተ-ፅህፈታዊው ምልክት መካከል አንድ ለአንድ የሆነ ግንኙነት የለም፡፡ በአብዛኛው የፅሁፋዊ ምልክቱ ቁጥር ከቀለሙ ቁጥር የበለጠ ነው፡፡

(ለ) ከምሳሌ (ሰ) እና (ረ) እንደምንረዳው የስርዓተ-ፅህፈታዊ ምልክቶች ተናጠል ድምፆችን ብቻ ሊያመለክቱ ይችላሉ፡፡ የምልክቶቹ ውክልና በእንግሊዝኛው አፃፃፍ እንደተመለከተው የቀለማዊ ቅንጅት ሳይሆን የተራ ድምፅ ዝርዝር ውክልና ነው፡፡


ከነዚህ ሁለት እውነታዎች ስለስርዓተ-ፅህፈቱ ሁለት አጠቃላይ ነገሮችን መገንዘብ ይቻላል፡፡

(1) እያንዳንዱ ስርዓተ-ፅህፈታዊ ምልክት የስነ-ልሳናዊውን ቀለም ክፊል (ሀ÷ለ) ወይም ሙሉ (መ) አካል ሊወክል ይችላል፡፡ በዚህ ደረጃ የእያንዳንዱ ምልክት ውክልና ለፎኒሞች ቅንጅት ነው፡፡ በቅንጅቱ ውስጥ የሚካተቱት ደግሞ የየቀለሙ ክፋች ተናባቢና አናባቢዎች ብቻ ናቸው፡፡ ስርዓቱን ቀለማዊ ሲያስኘው የኖረውም ይህ ቅንጅትን የማመልከት ተግባሩ ነው፡፡

(2) ቅንጅትን የሚያመለክተው ግን እንደ ምሳሌ (ሀ) እና (ለ) ባሉ ክፋች ተናባቢ ባላቸው ቀለሞች ውስጥ ነው፡፡ እንደ ምሳሌ (ሰ) እና (ረ) ባሉ

ቀለሞች ውስጥ ከፋች ተናባቢ ስለሌለ ስርዓተ-ዕህፈታዊው ምልክት የሚወክለው የየቀለሙን አናባቢና ከሱ ቀጥሎ የሚመጡትን ተናባቢ ፎኒሞች ነው፡፡ እነዚህ ደግሞ ነጠላ ፎኒሞች እንጅ ቅንጅት አይደሉም፡፡ ይህ ነጠላ ፎኒሞችን የማመልከት ባህሪ የቀለማዊ ስርዓተ-ዕህፈት ሳይሆን የፊደላዊ ስርዓተ-ዕህፈት ባህሪ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ስርዓተ-ዕህፈቱ ፊደላዊ እንጅ ቀለማዊ ሊሆን አይችልም፡፡

እንደ ምሳሌ (ሀ) እና (ለ) ባሉ ቀለሞች ውስጥም ቢሆን አናባቢውን ድምፅ ተከትለው የሚመጡት ተናባቢዎች የሚወከሉት በመሠረቱ እንደተናጠል ድምፅ እንጅ እንደ ቅንጅት አይደለም፡ እንደ ቅንጅት ሊወከሉ የሚችሉት በስነ-ግጥም ውስጥ ምጣኔን ለማስተካከል ሲባል (አ) የሚለውን አናባቢ ስንጠቀም ነው፡፡ ባጭሩ ከስነ-ግጥም ውጭ ከአናባቢው ቀጥሎ የሚመጡት ተናባቢዎች የሚወከሉት በተናጠል ምልክት ነው፡፡ ሁኔታውን ግልጽ ለማድረግ የሚከተለውን`እንመልከት:-




ይህ መዋቅር የሚያመለክተው የአማርኛንና የመሰል ቋንቋዎችን ስነ-ልሳናዊ ቀለም ይዘትና አቀነጃጀት ነው፡፡ በዚህ ውስጥ እንደ ቅንጅት በስርዓተ-ዕህፈታዊ ምልክት የሚወከሉት በማዕዘኑ ውስጥ የተመለከቱት ሁለት ፎኒሞች ብቻ ናቸው፡፡ ከማዕዘኑ ውጭ የሚታዩት ተናባቢዎች በተራ አጠቃቀም ጊዜ (ከስነ-ግጥም ውጭ) የሚወከሉት እንደ ተራ ፎኒም ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ስርዓተ-ዕህፈቱ ፊደላዊ መሆኑን በውል የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ስለስርዓተ-ዕህፈቱ ፊደላዊነት ይህን ያህል ከተገነዘብን ከዚሁ ጋር ወደተያያዙ ሌሎች ሁለት ጉዳዮች እንሂድ፤ ጉዳዮቹ ስርዓተ-ዕህፈቱ ከሚጠቀምባቸው ምልክቶች መጠንና ካጠቃቀማቸው ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ አማርኛ የሚጠቀምባቸው ምልክቶች ቁጥር ከፎኒሞቹ ቁጥር ጋር ሲነፃፀር እጅግ ብዙ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው የፎኒሞቹ ቁጥር በዛ ሲባል 38 አነሰ ሲባል ደግሞ 34 ነው፡፡ ስርዓተ ዕህፈቱ የሚጠቀምበት የምልክት መጠን ግን ቢያንስ ወደ 23 ይደርሳል፡፡ ይህ ፊደላዊ ስርዓተ-ዕህፈት አላቸው ከሚባሉት የምዕራባውያን ቋንቋዎች ፊደሎች ቁጥር ጋር ሲነፃፀር እጅግ ብዙ ነው፡፡

ጥያቄው ታዲያ የአማርኛው ስርዓተ-ዕህፈት ፊደላዊ ከሆነ ምልክቶች ይኸን ያህል ለምን በዙ? የሚል ነው።

እንደ ፎኒሞቹ 38 ብቻ ነው። እንደገና እንያቸው:-
በመሠረቱ ፎኒሞቹን የሚወክሉት የስርዓተ-ዕህፈቱ ምልክቶች ቁጥር ልክ

ሀ ል ም ስ ር ሽ ቅ ብ ት
ች ን ኝ ክ ው ዝ ዥ ይ ድ
ጅ ግ ጥ ጽ ጭ ፅ ዕ ፍ ፐ
ኰ ጐ ቈ ሆ አ ኡ ኢ ኣ ኤ

እነዚህ ተራ ፎኒምን የሚያመለክቱ ተራ ምልክቶች (ፊደሎች) ናቸው። ከዚህ ስንነሳ የፊደሎቹ (የምልክቶቹ) ቁጥር ብዙ አይደለም። ይህ ከግዕዝ የመጡትንና በአማርኛ ምንም ፎኒም የማይወክሉትን እንደ ሐ፥ሠ፥ኃ፥ጸ ያሉትን ትርፍ ፊደሎች ሳንጨምር ነው። አማርኛ የግዕዝን ስርዓተ-ዕህፈት የወሰደው ከነሙሉ ምልክቶቹ እንጅ ለእሱ የሚበጁትን መርጦ የማይበጁትን ትቶ አይደለም፤ (ዝርዝሩን ከባዬ፥ 1984)።

የፎኒሞቹና የምልክቶቹ ቁጥር እኩል ነው ካልን፥ 231 የሚለው የምልክቶቸ መጠን ከየት መጣ? ይህ አህዝ ከፎኒሞቹ ቁጥር ጋር ሳይሆን ከስርዓተ-ዕህፈቱና ከስርዓተ-አፃፃፉ ባህሪ ጋር የተያያዘ ነው። ስርዓተ-ዕህፈቱ ፊደላዊ ይሁን እንጅ ስርዓተ-አፃፃፍ እንደ ሌሎች ተመሳሳይ ፊደላዊ ስርዓተ-ዕህፈቶች ተናጠላዊ ብቻ ሳይሆን ቅንጅታዊ የሆነ የፎኒም አወካከል ያለው ነው። ይህም ማለት በምሳሌ (ሀ) እና (ለ) እንደተመለከትነው የቀለሙን ከፋች ተናባቢና ከሱ ቀጥሎ የሚመጣውን አናባቢ ፎኒሞች አቀናጅቶ፥ የነዚሁ ተናጠላዊ ምልክቶች የሆኑትን ፊደሎችም እያንዳንዱ ፊደላዊ ምልክት እንደዚሁ አቀናጅቶ ቅንጅትን በቅንጅት የሚወክል ስርዓት ነው። እያንዳንዱ ፊደላዊ ምልክት በዚህ አይነት ሲቀናጅ የቅንጅቱ ቁጥር ፎኒሞቹን ከሚወክሉት ፊደሎች ቁጥር ሰባት ጊዜ ይበልጣል። ይህም የሚሆነው የሰላሳ አንዱ ተናባቢ ፎኒሞች ምልክቶች ከሰባቱ የአናባቢ ፎኒሞች ምልክቶች ጋር ሲቀናጁ ነው። (31x7 = 231)። ይህ ቅንጅታዊ የሆነ ስርዓተ-አፃፃፍ ነው የምልክቶቹን ቁጥር ወደ 231 ያደረሰው።

ተናጠል የፎኒም ምልክቶች (ፊደሎች) የአንድ አናባቢ ፎኒም ቅንጅትን ለማመልከት የየግል ምልክታቸውን አቻችለው ወደ አንድ ቅንጅታዊ ምልክት ወይም ስርዓተ-ዕህፈታዊ ቀለም ይለወጣሉ። የአለዋወጡ ሁኔታ እንደሚከተለው ነው:-

ፊደል፡ ብ ብ ብ ብ ብ ብ

ስርዓተ-ፅህፈታዊ

ቀለም በ ቡ ቢ ባ ቤ ቦ

ተቃናጅ

ፎኒም ብ + አ ብ + ኡ ብ + ኢ ብ + ኣ ብ + ኤ ብ + ኦ

ከምሳሌዎቹ እንደሚታየው የተናባቢው ፎኒም ምልክት (ብ) የግል ምልክቱን ትቶ የተቃናጁን አናባቢ ፎኒም ልዩ ምልክት ይወርሳል፡፡ ሁለቱ ነጠላ ፊደሎች በአንድ ላይ ተቀናጅተው እያንዳንዳቸው በተናጠል የሚወክሉዋቸውን ፎኒሞች ቅንጅት ይወክላሉ ማለት ነው፡፡

ይህ ሁኔታ ስርዓተ-ፅህፈቱን ባለ ሁለት ፈርጅ ያደርገዋል፡፡ በአንድ በኩል እያንዳንዱዋን ፎኒም በተናጠል ይወክላል፡፡ ይህ ስርዓቱን መደበኛ ፊደላዊ ያደርገዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የተናጠል ፎኒሞችን ምልክቶች አጣምሮ ወይም አቀናጅቶ ተናባቢና አናባቢ ፎኒሞችን በአንድ ቅንጅታዊ ምልክት ይወክላል፡፡ ከዚህ ስንነሳ ስርዓተ-ፅህፈቱ እንደ ምዕራባዊ ስርዓተ-ፅህፈቶች ፊደላዊ መሆኑንና፥ ግን ደግሞ እንደ እነዚህ ስርዓቶች ተናጠላዊ ብቻ ሳይሆን ቅንጅታዊ ውክልና ያለው መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ሁለተኛው፥ ማለትም ቅንጅታዊ ውክልናው ከሌሎች ፊደላዊ ስርዓተ-ፅህፈቶች የተለየ ያደርገዋል፡፡ ይህ ቅንጅታዊነቱ ነው ሌሎች ተመሳሳይ ስርዓተ-ፅህፈቶች የሌላቸውን ብዛት ያለው ምልክት ባለቤት ያደረገው፡፡ ባጭር ቃል ስርዓተ-ፅህፈቱ ፊደላዊ፥ ስርዓተ-አፃፃፉ ቅንጅታዊ ነው፡፡


ቅንጅታዊነቱ ደግሞ ከላይ እንደ ተመለከተው በተራ ተናባቢና አናባቢ ጥምረት ብቻ አይወሰንም፡፡ ከዚህ አልፎ በየቅንጅቱ ላይ አናባቢዎችን በመጨመር የቅንጅት ቅንጅት እስከ መፍጠር ይደርሳል፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉትን እንመልከት፡-

ቡ + አ ሱ + አ ሹ + አ ወዘተ.

ቧ ሷ ሿ

ቀደም ሲል እንደ ተመለከተው 'ቡ' ከ(ብ) እና ከ(ኡ) የተገኘ ቅንጅት ነው፡፡ በዚህ ቅንጅት ላይ (ኣ) የሚለውን አናባቢ ስንጨምር 'ቧ' ን እናገኛለን፡፡ (ብ) የ (ኡ)ን ልዩ ምልክት ወስዶ ከቀኝ እግሩ መሀል ላይ በመቀጠል 'ቡ' እንደሆነ ሁሉ÷ 'ቧ' ም የ'(ኣ)'ን ልዩ ምልክት ወስዶ ግራ እግሩን ማሳጠርና (ጡ) መሆን ነበረበት፡፡ 'ሷ' እና 'ሿ' ም እንደዚሁ (ሱ)÷ (ሹ) መሆን ነበረባቸው፡፡ እንደ ጌ÷ ቌ ወዘተ ያሉትም ከ(ጉ) እና (ቁ) ወዘተ ላይ የ(ኤ)ን ልዩ ምልክት በመኮረጅ (ጉ)÷ (ቁ) ወዘተ መሆን ነበረባቸው አካሄዱ ለምን እንደዚህ እንዳልሆነ ለጊዜው ምክንያት የለንም፡፡

ጠቅላላውን የድምፆችን ተናጠላዊና ቅንጅታዊ ስርዓት ግን እንደሚከተለው አድርጎ በኳ(ኩ) አማካኝነት ማሳየት ይቻላል




- ደረጃ ሁለት ቅንጅታዊ ውክልና
- ደረጃ አንድ ቅንጅታዊ ውክልና
- ተናጠላዊ ውክልና

ይህ ሁኔታ ስርዓተ-ፅህፈቱ ፊደላዊ ሆኖ ስርዓተ አፃፃፉ ተናጠላዊና ቅንጅታዊ መሆኑን÷ ቅንጅታዊነቱ ደግሞ ባለሁለት ደረጃ መሆኑን በግልፅ

ያመለክታል፡፡ አሁንም ሁኔታውን ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ <u>አንኳር</u> የሚለውን ቃል አፃፃፍ እንይ፡-

| | |
|---|---|
| አን - ኳ - ር | - ከፊል ግን ከፍተኛ ቅንጅታዊ አፃፃፍ |
| አን-ኩኣ-ር | - ከፊል ግን መለስተኛ ቅንጅታዊ አፃፃፍ |
| ኧ-ን-ክ-ኡ-ኣ-ር | - ተናጠላዊ አፃፃፍ |

የቅንጅታዊነቱ ደረጃ በጨመረ ቁጥር የምልክቶቹ መጠን እየቀነሰ ይሄዳል፡፡ ከፍተኛው የምልክት መጠን የሚታየው በተናጠላዊ አፃፃፍ ሲሆን ዝቅተኛው ደግሞ በከፍተኛው ቅንጅታዊ አፃፃፍ ነው፡፡

በተናጠላዊ ዘርፍ የሚመደቡት 38 ፊደሎች ብቻ ሲሆኑ በመለስተኛው ቅንጅታዊ ዘርፍ የሚመደቡት ደግሞ ስርዓተ-ፅህፈታዊ ቀለም የሚባሉት 231 ምልክቶች ናቸው:: በሶስተኛው ዘርፍ የሚመደቡት ደግሞ እንደ ቧ፣ ሷ፣ ሿ ያሉት ከፍተኛ ቅንጅቶች ናቸው:: 38ቱ ፊደሎች በፊደል ገበታ ላይ ሳድስ ተብለው የሚታወቁት ሲሆኑ፥ 231ዱ ደግሞ ባጠቃላይ ቀለም ዬሚባሉት ናቸው:: እነዚህን ቆጥሮ ሲጨርስ ተማሪው ቀለም ለየ ይባላል::


እንግዲህ ስርዓተ-ፅህፈቱ አንድ ተናጠላዊና ሁለት ቅንጅታዊ ደረጃ ያለው ፊደላዊ ስርዓት ነው ካልን የዚህ አንድምታ ምን ሊሆን እንደሚችል ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን::

## 3.1 አጻጻፍ

የመጀመሪያው አንድምታ በራሱ በስርዓተ-አፃፃፉ ላይ ነው:: ከፍ ሲል እንደ ተመለከተው አፃፃፉ በከፊል ተናጠላዊ በከፊል ደግሞ ቅንጅታዊ ነው:: በተለምዶው አፃፃፍ የዚህ ጽሁፍ አጠናቃሪ ስም የሚከተለውን ይመስላል::

ባዬ ይማም

በዚህ ውስጥ /ም/ በተናጠላዊ፥ ሌሎቹ ደግሞ በቅንጅታዊ ምልክቶች የተፃፉ ናቸው:: አቀነጃጀታቸው እንደሚከተለው ነው::




ቅንጅታዊው አፃፃፍ የአንዳንድ ፎኒሞችን ልዩ ባህሪ አያመለክትም ለምሳሌ ባዬ በሚለው ውስጥ (ይ) የሚለው ተናባቢ ፎኒም ጠባቂ ነው:: 'ዬ' የሚለው ቅንጅታዊ ምልክት ግን ይህን ጠባቂነቱን አያመለክትም:: ስለዚህም ቃሉን አንዱ አጥብቆ ሌላው ደግሞ አላልቶ ሊያነበው ይችላል:: ይህ በተለይ ቋንቋዋውን ለማያውቁ ሰዎች ችግር እንደሚፈጥር ግልፅ ነው:: ይህ አይነቱ የተለያየ አነባበብ በዚህ ቃል ላይ ባይሆንም እንደ 'ገና' ባሉ ሌሎች ቃላት ላይ የትርጉም ለውጥን ያስከትላል:: በቅንጅት የሚመለከት ፎኒም ስርዓተ-ፅህፈታዊ ቅርጹ አንድ ሆኖ ንበታዊ ቅርጹ ሁለት አይነት ሊሆን ይችላል ማለት ነው:: ይህ ሁኔታ በአማርኛ ብቻ ሳይሆን በብዙዎቹ የሀገራችን ቋንቋዎችም ስለሚታይና ስርዓተ-ፅህፈቱም ከዚሁ ሁኔታ ጋር

እንዲጣጣም ስላልተደረገ፥ ከፍ ሲል እንደተገለፀው፥ በተለይ ተወላጅ ላልሆኑ ተናጋሪዎች የአነባበብ ችግር መፍጠሩ አልቀረም። ቀደም ሲል ከተጠቀሰው የምልክት ብዛት ላይ ይህ ሲጨመር ስርዓተ-ዕህፈቱን አስቸጋሪ ሊያሰኘው ችሎአል።

ይህ የአፃፃፍ ችግር ግን ከስርዓተ-ዕህፈቱ ሳይሆን ከስርዓተ-አፃፃፉ ፈርጅ የመነጨ ነው። ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው ስርዓተ-ዕህፈቱ ተናጠላዊና ቅንጅታዊ ፈርጅ አለው። ጥብቀትንና ሌሎችንም የድምፅ ባህሪያትን በተለመደው ቅንጅታዊ አፃፃፍ ማመልከት አይቻልም። ይህ አይነቱ ችግር የሚፈታው በስርዓተ-አፃፃፍ ብቻ ሳይሆን፥ በባዬ (1984) እንደተገለጸው በስርዓተ-አገባብ ነው። ለምሳሌ በሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ 'ገና' የሚለውን ቃል አገባብ እንመልከት፡-

1. (ሀ) አቶ ካሳ ገና በግ አልገዙም
   (ለ) አቶ ካሳ ለገና በግ አልገዙም

በመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ውስጥ ያለው 'ገና' የጊዜ ተውሳከ ግስ ነው። በሁለተኛው ዐረፍተ ነገር ውስጥ ያለው 'ገና' ደግሞ ስም ነው። ከዚህ የቃላት ክፍል ልዩነት የተነሳ ያገባብ ልዩነትም በሁለቱ ቃላት መካከል አለ። ይኸውም በሁለተኛው ዐ.ነገር ውስጥ ያለው 'ገና' በስምነቱ የተዋቀረው መስተዋድድ ከሆነው ከ'ለ' ጋር ሲሆን፥ በመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ደግሞ በተውሳከ ግስነቱ፥ መዋቅራዊ ግንኙነቱ ከግሳዊ ሀረጉ ጋር ነው። ከዚህ የክፍል እና የአገባብ ልዩነት በመነሳት የሁለቱን ቃላት ንበት መለየት ይቻላል። ቅንጅታዊው ስርዓተ-አፃፃፍ የሚፈጥረውን አሻሚነት ስርዓተ-አገባብ ይፈታዋል ማለት ነው።

ከአገባቡ ሳይሆን ከራሱ ከእያንዳንዱ ቃል ተናጠላዊ አቀዋም የድምፆችን የመጥበቅ ወይም የመላላት፥ የመርዘም ወይም የማጠር፥ ወዘተ. ባህሪ ስርዓተ-ዕህፈቱ ማሳየት እንዲችል ከተፈለገ አፃፃፉን ቅንጅታዊ ሳይሆን ተራ ፊደላዊ (ተናጠላዊ) ማድረግ ያስፈልጋል። የስርዓተ-ዕህፈቱን ሁለተኛ ፈርጅ፥ ማለትም ተናጠላዊነቱን መጠቀም የግድ ይሆናል ማለት ነው። በዚህ ፈርጁ ስንጠቀም ከላይ የተጠቀሱት ዐ.ነገሮች እንደሚከተለው ሆነው ይፃፋሉ፡-

2. (ሀ) ኣትእ ከኣስኣ ግእንኣ ብእግ ኣልግእዝዝኡም

(ለ) ኣትእ ከኣስኣ ልእግእንንኣ ብእግ ኣልግእዝዝኡም

ይህ ስርዓተ-አፃፃፍ ፎኒሞች እየተቀናጁ በአንድ የተቀናጀ ምልክት የሚወከሉበት ሳይሆን እያንዳንዳቸው በተናጠል በነጠላ ምልክት (ፊደል) የሚታዩበት ነው። ስርዓተ አፃፃፉ የጠባቂ ፎኒሞችን ጥብቀት ምልክቱን ደግሞ በመፃፍ ማሳየት ይችላል። በዚህ አይነት አማርኛን ብቻ ሳይሆን ማንኛውንም የሀገራችን ቋንቋዎ መጻፍ ይቻላል። ለምሳሌ የተናባቢ ጥብቀት ብቻ ሳይሆን የአናባቢ ርዝመት ያላቸውን የኩሸ፥ የኦሞና፥ የአባያዊ ቋንቋዎችን የሚረዝመውን አናባቢ ምልክት ደግሞ በመጻፍ መለየት ይቻላል። ለአብነት ያህል የሚከተሉትን እንመልከት፡-

3. ( ሀ) ኣት ምኣትእኦትትኦ (ሃዲያ፡ Stinson, 1976)

'ትሄዳለህ'

(ለ) ኢ ከኣኣልልኢስ (ወላይታ፡ Ohmantal (1976:155))

'ተከተለ'

በሁለቱም ምሳሌዎች ውስጥ እንደሚታየው እያደረጉ የፎኒሞችን ልዩ ባህሪያት ማመልከት ይቻላል፤ ስርዓተ-ፅህፈቱ እንደማንኛውም ፊደላዊ ስርዓተ-ፅህፈት ፎኒሞችን በተናጠል ምልክት ከላይ እንደሚታየው እያደረገ የማመልከት ችሎታ አለውና።

ይህ አይነቱ ተናጠላዊ አፃፃፍ ግን ሶስት ችግሮች አሉበት። አንደኛው ቦታ ፈጅ መሆኑ ነው። እያንዳንድዋን ፎኒም ከነልዩ ባህሪዋ በተለየ ምልክት ስንወክል ብዙ ቦታ እንፈጃለን። ለዚህ የሚከተለውን የአማርኛ ምሳሌ ፊደላዊ (ተናጠላዊ) አፃፃፍ ከተለመደው አፃፃፍ ጋር እያነፃፀርን እንመልከት፡-

4. (ሀ) ኣበበ እንደ ከበደ ኣካሄዱን ኣላወቀበትም

አፃፃፍ፤ ቅንጅታዊና ተናጠላዊ

የምልክት ብዛት 21

(ለ) ኣብአብአ እንድአ ክአብብአድአ ኣክክአህኤድኡን
አልኣውውአቅአብብአትም

አፃፃፍ ሙሉ በሙሉ ተናጠላዊ

የምልክት ብዛት 39

በተለምዶው ኣፃፃፍ 21 ቦታ የወሰደው ዐረፍተ ነገር በተናጠል ምልክት ሲፃፍ 39 ቦታ ሊወስድ ችሎአል። ከህትመት ኣንፃር ሲታይ የሚፈጀው ወረቀትና ገንዘብ ቀላል አይደለም። ይህ እንግዲህ የስርዓተ-አፃፃፉ ኢኮኖሚያዊ እንድምታ ነው።

ሁለተኛው ችግር በተናጠላዊ ምልክት የሚፃፉ ቃላት ለዐይን ረዥም መሆናቸው ነው። ለዚህ 'ከበደ'ን ከ'ክአብብአድአ' ጋር ማነፃፀር ይቻላል። 'ከበደ' አጭር ስለሆነ ለዐይን ማለትም ለዕይታ ይቀላል። ይህ በተለይ ማንበብና መፃፍ ገና በሚለማመዱ ተማሪዎች ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ ቀላል አይሆንም።

ሶስተኛውና ትልቁ ችግር ከቋንቋው ተጠቃሚዎች ስነ-ልሳናዊ ችሎታ ጋር የተያያዘ ነው። ማንኛውም የአንድ ቋንቋ ተወላጅ ተናጋሪ የዚያ ቋንቋ ዕውቀት አለው። ስለዚህ ዕውቀት ያለው ግንዛቤም እስከ ድምጽ ድረስ ነው። ይህም ማለት ማንኛውም የአንድ ቋንቋ ተወላጅ ተናጋሪ ቃላትን፥ በቃላት ውስጥ ስነ-ልሳናዊ ቀለማትን፥ በቀለማት ውስጥ ደግሞ ድምፆችን የመለየት ችሎታ አለው። በየፎኒሞቹ ውስጥ የሚገኙ እንደ ጥብቀት፥ ርዝመት፥ ድምጸት ወዘተ. ያሉ ባህሪያትን ግን አይገነዘብም። ከአጠቃላይ ቃላዊ ዕውቀቱ ረዥም አናባቢ ያለበትን ቃል አጭር አናባቢ ካለበት ሌላ ቃል የመለየት ችሎታ እንጂ በቃሉ ውስጥ ያለ ረዥምና አጭር ፎኒምን የመለየት ችሎታ የለውም። ለምሳሌ 'ሽልማት' በሚለው ቃል ውስጥ ያለው 'ል' ጥብቅ 'ል' ነው። ይህን ፎኒም አላልተን ቃሉን ለአንድ ተወላጅ የአማርኛ ተናጋሪ ብንልለት ቃሉን በትክክል እንዳልተናገርነው ይነግረናል። ከዚያ አልፎ ግን 'ል'ን አጥብቅ ብሎ አያርመንም። ቃሉ ትክክል አለመሆኑን እንጂ ትክክል ያለመሆኑን ምክንያት አይነግረንም። በአጭሩ ማንኛውም ሰው የቃል እንጂ የድምፀ ባህሪ ግንዛቤ የለውም።

ይህን ለማረጋገጥ የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ በሚያስተምረው የትምህርት ክፍል ELAM 307 የሚባለውን የአማርኛ መዋቅር ትምህርት በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ተደጋጋሚ ሙከራ አካሂዶ ነበር። በሙከራው የተወሰኑ ቃላትን ከላይ

በተመለከተው አይነት በተናጠላዊ አፃፃፍ እየፃፉ ጥብቅ ተናባቢዎችን ማመልከት ነበር። በሙከራው የተገኘው ከፍተኛ አማካኝ ውጤት 6 ከ 10 ነበር። ስህተቶቹ አንድ ወጥ አልነበሩም። አንዱ ያጠበቀውን ሌላው ያላላዋል። በዚህ አይነት ከተፃፉት ቃላት መካከል አንዱ 'እንክት' የሚለው ነበር። ይህን ቃል አንዳንዶቹ [እንክክት]፥ አንዳንዶቹ [እንክትት]፥ አንዳንዶቹ ደግሞ [እንክት] አድርገው ሲፅፉት አንድ ተማሪ ብቻ [እንክክእትት] ብሎ በትክክል ፅፎታል። እነዚህ በዩኒቨርስቲ ደረጃ ቋንቋውን እየተማሩ ያሉና መሠረታዊ የስነ-ልሳን ትምህርት ያላቸው ናቸው። እነሱ በትክክል የየድምፁን ባህሪ መገንዘብና በትክክል ማመልከት ከተሳናቸው ሌላው ተራው ፀሃፊ ምን ሊያደርግ እንደሚችል መገመት ይቻላል።

ማንኛውም ከላይ በተመለከተው አይነት የሚፅፍ ሰው ተማሪዎቹ እንዳደረጉት በየቃሉ ውስጥ ያለውን ተናባቢ ይጠብቃል ወይስ አይጠብቅም እያለ መጠየቅ ወይም ለዚህ የተዘጋጀ መዝገበ ቃላት ካለ እሱን ማገላበጥ ይኖርበታል። በአጭር ቃል በእንግሊዘኛ ስንፅፍ የሚገጥመን አይነት የሆሄ (spelling) ችግር በአማርኛው ይገጥመዋል[4] ። በዚህ ረገድ በላቲን በሚፃፉ ቋንቋዎች ላይ ተመሳሳይ ጥናት ማድረግ ተገቢ ይሆናል። ሁኔታው የሚጠቁመው የትምህርቱ ይዘት በፊደል ቆጠራ ብቻ ሳይወሰን አፃፃፍንም መጨመር ያለበት መሆኑን ነው።

እስካሁን ከተጠቀሱት ችግሮች ለመዳን ሁለት አማራጮች አሉ። አንደኛው፥ እንደተለመደው ስርዓተ-ዕህፈቱን በቅንጅታዊ ፈርጁ መጠቀምና ከድምፅ ባህሪያት የተነሳ የሚከሰተውን የአሻሚነት ችግር ቀደም ሲል እንደተመለከተው በየቃሉ አገባብ መፍታት ነው። በዚህ ደረጃ የስርዓተ-ዕህፈቱ ቅንጅታዊ ምልክቶች ሙሉውን ቃል አስታዋሽ እንጂ በየቃሉ ውስጥ ያለውን የየድምፅ ባህሪ ወካይ አይሆኑም። ስለዚህም 'እንክት' የሚለውን ስርዓተ-ዕህፈታዊ ቅርጽ ስናይ ሙሉውን ቃል እናስታውስና እንደምናውቀው አድርገን እናነበዋለን። በዚህ ደረጃ የየቃሉ ንበታዊ ቅርጽና ስርዓተ-ዕህፈታዊ ቅርጽ በከፊል ይለያያሉ፤ የስርዓተ-ዕህፈታዊ ምልክቶች የድምጾችን ልዩ ባህሪያት ስለማይወክሉ። ይህ አማራጭ ቢያንስ በአማርኛ በተለመደ መልኩ ሊቀጥል ይችላል።

[4] የእንግሊዘኛው ኣፃፃፍ ችግር በፊደሎቹና በሚወክሉኣቸው ድምፆች መካከል ያለው ልዩነት ነው። ለምሳሌ through የሚለው ቃል ሰባት ፊደሎችን የያዘ ሲሆን የሚወክሉት ድምፆች ግን ሶስት ብቻ ናቸው።


ሁለተኛው አማራጭ የስርዓተ-ፅህፈቱን ሁለት ፊርጀች መጠቀም ነው። ይህም ተናጠላዊ ውክልና በሚያስፈልግበት ሁኔታ ብቻ ፎኒሞችን በተናጠል እያመለከቱ፥ ይህ ሁኔታ በሌለበት ጊዜ ደግሞ በቅንጅት በማመልከት ነው። ይህ አማራጭ ቀደም ሲል የተጠቀሱትን የኢኮኖሚና የእይታ ችግሮቸ በሙሉ፥ እንዲሁም በጥብቀትና በርዝመት ምክንያት የሚከሰቱ የአሻሚነት ችግሮችን በከፊል ይፈታል። ከዚህ አንፃር ቀደም ሲል በተራ ቁጥር (4ለ) በተናጠል ምልክቶች የፃፍነውን ዐረፍተ ነገር በዚህ በሁለተኛው አማራጭ ብንፅፈው የሚከተለውን ይመስላል።

(5) ካሳ እንደ ከብበደ አክካሄዱን አላውወቀብበትም

የምልክት ብዛት 24

በዚህ አይነት አፃፃፍ መጥበቅና መርዘም ያለባቸው ፎኒሞች ብቻ በተናጠል ምልክቶች ሲወከሉ ሌሎቹ በተለመደው ቅንጅታዊ አፃፃፍ ይወከላሉ።

ይህ አማራጭ ቀደም ሲል ከጠቀስነው የአፃፃፍ (የሆሄ) ችግር ሙሉ በሙሉ ነጻ አይደለም። አሁንም የሚጠብቁና የሚረዝሙ ፎኒሞችን የመለየት ችግር ይኖራል። ይኑር እንጅ ደረጃው ያንሳል። ሁሉንም ቃላት በተናጠል ምልክት ስለማንፅፍ ይጠብቃል ወይስ አይጠብቅም የሚለው ጥያቄ በተወሰኑ በተናጠል ምልክቶች በሚጻፉ ፎኒሞች ላይ ብቻ ይሆናል። ለምሳሌ ከላይ በተራ ቁጥር (5) እንደተመለከተው ከበደ በሚለው ስም ውስጥ ያለውን (ብ)፥ አካሄድ በሚለው ውስጥ ያለውን (ከ) እና አላወቀበትም በሚለው ውስጥ ያሉትን (ው) እና (ብ) በተናጠል ምልክቶች እያመለከቱ ሌሎቹን ፎኒሞች በቅንጅት መወከል ይቻላል። በተናጠል ምልክቶች የሚወከሉትም ቢሆኑ ያወካከሉ የተናጠልነት ደረጃ ከፊል ነው። ለምሳሌ ከበደ በሚለው ስም ውስጥ ያለው (ብ) ጠባቂ መሆኑን የምናመለክተው ከብበደ ብለን በመፃፍ ነው። ሁለተኛው (ብ) ተከትሎት ከሚመጣው አናባቢ ማለትም ከ(አ) ጋር ተቀናጅቶ 'በ' ሆኖአል። በተናጠል ቢጻፍ ኖሮ ቃሉ (ከአብብአድአ) ይሆን ነበር። በተናጠል መወከል ያለበትን አስቀርተን መቀናጀት የሚችለውን ስናቀናጅ ቃሉ እንደሚከተለው ይሆናል፦



ያልተቀናጀችውና የ'በ'ን መጥበቅ የምትጠቁመን (ብ) ነች። በዚህ አይነት ስርዓተ-አፃፃፍን በከፊል ቅንጅታዊ በከፊል ደግሞ ተናጠላዊ ማድረግ ይቻላል። ከዚህም አልፈን ማንኛውንም ጠብቆ የሚነገርን ፎኒም ሳይሆን የትርጉም አሻሚነትን ሊያስከትል የሚችልን ፎኒም ብቻ በተናጠል ፊደል እያመለከትን የአሻሚነት ችግር የማያስከትለውን ማንኛውንም ፎኒም በመደበኛው ቅንጅታዊ ምልክት መጻፍ ይቻላል። እንደዚህ እያደረጉ መፃፍ የሚጠብቀውንና የማይጠብቀውን ፎኒም ካለመለየት ሊከሰት የሚችልን የአፃፃፍ ስህተት መጠን ይቀንሳል። ባጭሩ ተናጠላዊውን አፃፃፍ እንደ ገና ላሉ አሻሚ ቃላት ብቻ መወሰን ይቻላል።

ከዚህ የምንረዳው ስርዓተ-ዕህፈቱ ሲፈለግ የሚነጠል፥ ሲፈለግ ደግሞ የሚታጠፍ ባለሶስት ፈርጅ ስርዓት መሆኑን ነው። ይህም ባህሪው ከሌሎች ስርዓተ-ዕህፈቶች ጋር አንድም ልዩም ያደርገዋል። በአንድነቱ፥ ተናጠል ፎኒሞችን በተናጠል ምልክት ሊወክል ይችላል። በልዩነቱ ደግሞ በተናጠል ሊወክል የሚችላቸውን ፎኒሞች በሁለት ወይም በሶስት እያቀናጀ በአንድ ቅንጅታዊ ምልክት ይወክላቸዋል። ተናጠላዊ ውክልናው ቦታ ፈጅና ለዕይታና ለአፃፃፍም አስቸጋሪ ሲያደርገው ቅንጅታዊ ውክልናው ደግሞ ቁጥብ ግን አሻሚ ያደርገዋል። አሻሚነቱ የቅርፅ ወይም የትርጉም ሊሆን ይችላል። በቅርፅ ደረጃ ያለው አሻሚነት በአንድ ቃል ውስጥ ያለ አንድን ድምፅ ላልቶ ወይም ጠብቆ እንዲነበብ ሊያደርገው ይችላል[5] ። እንደዚህ አድርጎ ማንበቡ ግን የቃሉን ትርጉም አይለውጠውም፤ የሚለውጠው ንበታዊ ቅርጹን ብቻ ነው። ከፍ ሲል ያየነው ገና የሚለው ቃል ግን እንደ ንበታዊ ቅርፁ ትርጉማዊ ይዘቱም ይለወጣል። ስርዓተ-ዕህፈቱ በንጥላዊነቱ የሆህያትና የቦታ ፈጅነት፥ በቅንጅታዊነቱ የአሻሚነት ችግሮች አሉት። ሁለቱን ችግሮች ለማመናመን የትርጉም አሻሚነት በሚያስከትሉ ቃላት ውስጥ ብቻ ተፈላጊውን ፎኒም በተናጠላዊ ምልክት እየወከሉ ሌሎቹን ፎኒሞች በቅንጅታዊ ምልክት መፃፍ የተሻለ አማራጭ ነው። ይህን ሶስተኛውን አማራጭ ቀቤና (ከምባትኛ) የሚባለው የኩሽ ቋንቋ እየተጠቀመበት ነው። እስካሁን ድረስ በትምህርቱ ላይ ከስርዓተ-ዕህፈቱ የመነጨ ችግር ጉዳዩን ለሚከታተለው ለስነ-ልሳን ክፍል አልደረሰም። አይድረስ እንጅ የቋንቋዋው ተጠቃሚዎች ጥብቅና ልል፥ እንዲሁም ረዥምና አጭር አናባቢዎችን የመለየት ችግር እንደሚገጥማቸው ዕውቅ ነው፤ መጠነኛ ቢሆንም።

[5] ላላልቶ የሚያነበው አማርኛን በወጉ የማያውቅ ነው። አማርኛን በሚገባ የሚያውቅ ሰው ላላልቶ ለማንበብ ይቸገራል። ቃሉን የሚያውቀው ከነጥብቀቱ ነውና።

እስካሁን የተመለከትነው የስርዓተ-ዕህፈቱ ተናጠላዊነትና ቅንጅታዊነት በአፃፃፍ ላይ ያለውን ወይም ሊኖረው የሚችለውን አንድምታ ነው። አንድምታው አፃፃፋችንም እንደ ስርዓተ-ዕህፈቱ ተናጠላዊ ወይም ቅንጅታዊ፥ ወይም ደግሞ ከፊል ቅንጅታዊና ከፊል ተናጠላዊ ሊሆን መቻሉን ነው። ይህ ከሆነ እስካሁን በዕሁፍ ላይ ገና ያልዋሉ የሀገራችን ቋዋንቋዋዎች በዚህ ስርዓተ-ዕህፈት ቢጠቀሙ ሶስት የስርዓተ-አፃፃፍ ምርጫ ይኖራቸዋል። ከፍ ሲል የተጠቀሰው የቀቤና ቋዋንቋዋ ከነዚህ ምርጫዎች ከፊል ቅንጅታዊ ከፊል ተናጠላዊ የሆነውን ስርዓት መርጦአል። ወደ ሌላው የስርዓተ-ዕህፈቱ አንድምታ እንሂድ።

## 3.2 ትምህርት

በዚህ ላይ የስርዓተ-ዕህፈቱ ቀጥተኛ አንድምታ በፊደል ትምህርት ላይ ነው። ብዙዎቻችን ባለፍንበት የቄስ ትምህርት ቤት የፊደሉ ትምርት 'ሀ ሁ'ን፥ ሁ-ግዕዝ ሁ-ካዕብንና አቡጊዳንና[6] መልዕከተ ቁጥርን ያካትታል።[7] እነዚህ እንደቅደም ተከተላቸው ፊደል ቆጣሪው እያለፈና እየተከለሰ የሚደርስባቸው ደረጃዎች ናቸው። በነዚህ ውስጥ ተማሪው የስርዓተ-ዕህፈቱን ምልክቶች መለየት እንጅ ማንበብ አይችልም። የንባብ ደረጃ የሚጀምረው በመልእክተ ግዕዝ ነው።

የፊደል ቆጠራው ትምህርት የሚቀርበው በፊደል ገበታ (ፊደለ ሀዋርያ) ሲሆን፥ ይዘቱም ሆነ አቀራረቡ በደረጃ ያልተመጠነ አንድ ወጥ ነው። በዚህ ውስጥ አስቸጋሪው ትምህርት የሳድሶቹ ቅርጽ ነው። እንደ ሌሎቹ ህገኛ አይደሉም። የማስተማር ዘዴውም ከስንጥር መጠንቆያና ከማስፈራሪያ አለንጋ ያለፈ አይደለም።

በዘመናዊ (አስኮላ) ትምህርትም ቢሆን የትምህርቱ ይዘት በመሠረቱ ከቄሱ ትምህርት ቤት የተለየ አይደለም። በዚህም ቢሆን የሚቀርበው ትምህርት አንድ ወጥ ነው። ከግዕዝ እስከ ሳብዕ፥ ከ'ሀ' እስከ 'ፐ' ያለው ዝርዝር እንደተጠበቀ ሆኖ አቀራረቡ ብቻ በአንድ የፊደል ገበታ የሚጠቃለል ሳይሆን በትንሽ በትንሹ የሚመጠን ነው። እያንዳንዱ ምልክትም በስንጥር የሚጠነቆል ብቻ ሳይሆን በእርሳስ እየተጻፈ የሚለይም ነው። እንዲዚህም ሆኖ የሳድሶቹ ህገ-ወጥነት አሁንም ለተማሪዎች አስቸጋሪው ክፍል ነው።

---

[6] ለዝርዝሩ ሃይለገብርኤል (1968፥1971) ይመልከቱ።

[7] የአቡጊዳ ትምህርት ፊደሎች ሁሉ ተዘበራርቀው የሚቀርቡበት ስለሆነ በጣም አስቸጋሪ ነው። በዚህም ምክንያት 'አቡጊዳ ሄው!፣ ልጄን ገደለው ወዝውዞ' ይባላል።

ይህን ችግር ለማቃለል አንዳንድ እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡ ከነዚህ መካከል በዕድገት በህብረት ዘመቻ ጊዜ የፊደሉን ተዋረዳዊ ቅደም ተከተል ከሀ፥ ለ፥ ሐ ፥ መ . . . ወደ በ፥ ሰ፥ ሸ . . . መለወጥና ሳድሶቹን ደግሞ ከሌሎቹ ለይቶ ለብቻ ማስተማር ዋናዎቹ ናቸው፥ እነዚህ እርምጃዎች የተወሰዱት ከስነ-ዘዴ አንጻር ነው፡፡ የሳድሶቹ ከሌሎቹ ምልክቶች መለየት ግን ስነ-ዘዴያዊ ብቻ አልነበረም፡፡ ለስነ-ዘዴው መንስዔ የሆነ ስነ-ልሳናዊ መሠረት አለው፡፡ ይህም በዚህ ጽሁፍ እያየነው የመጣነው የስርዓተ-ዕህፈቱ ፊደላዊነት ነው፡፡ ፊደላዊነቱ ደግሞ እንደሌሎች ተመሳሳይ ስርዓቶች ባለ አንድ ሳይሆን ባለሁለት ፈርጅ ነው፡፡ አንደኛው ተናጠላዊ ሁለተኛ ቅንጅታዊ ነው፡፡ ተናጠላዊው ፈርጅ እያንዳንዱ ፎኒም በተናጠል የሚወከልበት ሲሆን ቅንጅታዊው ደግሞ ተናጠላዊ ምልክቶቸ በሁለት ደረጃ የሚጣመሩበት ነው፡፡ ህገ-ወጥ የምንላቸው ሳድሶች የተናጠላዊው ፈርጅ ክፍል ሲሆኑ ሌሎቹ የቅንጅታዊው ፈርጅ ክፍል ናቸው፡፡ ቅንጅት የሆኑት በአብዛኛው አንድ አይነት ያቀነጃጀት ስርዓት ስለሚከተሉ ተመሳሳይ አካሄድ አላቸው፡፡ ሳድሶቹ ግን ቅንጅት ሳይሆኑ ተናጠል ፎኒሞችን የሚወክሉ ልዩና ተናጠል ምልክቶች ናቸው፡፡ በዚህም፥ ተመሳሳይ አቀነጃጀት ከሚከተሉት፥ ከቅንጅቶቹ ሊለዩ ችለዋል፡፡ ይህ ልዩ ልዩ የመሆናቸው ነገር ነው ህገ-ወጥ የሚያሰኛቸው፡፡ በመሠረቱ ግን ህገ-ወጥ አይደሉም፡፡ እያንዳንዳቸው የተለያዩ ፎኒሞችን ስለሚወክሉ የተለያየ ቅርጽ መያዛቸው ተገቢ ነው፡፡ ተገቢ ያልሆነው እነዚህን የተለያየ ቅርጽና ደረጃ ያላቸውን ተናጠላዊ ምልክቶች ተመሳሳይ አካሄድ ካላቸው ቅንጅቶች ጋር በአንድ ላይ አጠቃሎ ለትምህርት ማቅረቡ ነው፡፡

ከዚህ ስንነሳ የፊደሉ ትምህርት እንደ ስርዓተ-ዕህፈቱ ባለሁለት ደረጃ መሆን እንዳለበት እንረዳለን፡፡ የመጀመሪያው ደረጃ ተናጠል ፎኒሞች የሚወክሉት ተናጠል ምልክቶች ብቻ የሚገኙበት ሲሆን ይህን ተከትሎ የሚመጣው ደግሞ የተናጠሎቹ ቅንጅት የሆኑት ምልክቶች የሚቀርቡበት ነው፡፡ እነዚህን ሁለት ደረጃዎች የፊደልና የቀለም ብለን እንለያቸዋለን፡፡ አቀራረባቸውም በዕድገት በህብረት ጊዜ እንደተጀመረው ከቀለም ወደ ፊደል ሳይሆን ከፊደል ወደ ቀለም ነው፡፡

የፊደሉ ትምህርት አቀራረብም በሁለት መርሆች ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡ የመጀመሪያው መርህ ፊደሎቹ የሚወክሉዋቸው ድምጾች ስርጭታዊ ደረጃ ነው፡፡ በማንኛውም ቋዋንቋዋ የሚገኙ ድምጾች እኩል ስርጭት የላቸውም፡፡ አንዳንዶቹ እጅግ በርካታ፥ አንዳንዶቹ ጥቂት፥ አንዳንዶቹ ደግሞ እጅግ ውሱን በሆኑ ቃላት ውስጥ ብቻ ይገኛሉ፡፡ በዚሁ መሠረት ከፍተኛ ስርጭት ያላቸውን ድምጾች የሚወክሉት ምልክቶች አነስተኛ ስርጭት ያላቸውን ድምጾች ከሚወክሉ ምልክቶች ቀድመው ለትምህርት መቅረብ አለባቸው፡፡

እንደዚህ ያሉ ምልክቶችን ቀድሞ ማወቁ ተማሪውን ገና ከመነሻው በርካታ ቃላትን እንዲያነብ ይረዳዋል፡፡

በዚህ መሠረት የአማርኛን ድምፆች የስርጭት ደረጃ ለመወሰን ሰባት የአዲስ ዘመን ርዕሰ-አንቀጾችን በመውሰድ እያንዳንዱ ድምፅ በነዚህ ርዕሰ-አንቀጾች ውስጥ ስንት ጊዜ እንደተደጋገመ ለማወቅ ተሞክሮአል፡፡ በውጤቱ መሠረት የድምጾቹ ቅደም-ተከተል እንደሚከተለው ነው፡፡[8] ዝርዝሩን አባሪ (1) ላይ ይመልከቱ)

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተናባቢ፡- | ም÷ | ት÷ | ን÷ | ል÷ | ብ÷ | ር÷ | ይ÷ | ው÷ |
| | ስ÷ | ግ÷ | ድ÷ | ክ÷ | ች÷ | ጥ÷ | ቅ÷ | ህ÷ |
| | ፍ÷ | ዝ÷ | ጅ÷ | ኝ÷ | ሽ÷ | ፅ÷ | ጭ÷ | ዕ÷ |
| | ፕ÷ | ዥ÷ | ጎ÷ | ኰ | ዅ÷ | (ቆ)÷ | | ጵ |
| አናባቢ÷ | አ÷ | ኣ÷ | እ÷ | ኡ÷ | ኢ÷ | ኦ÷ | | ኤ |

በዚህ መሠረት የፊደሉ ቅደም ተከተል በ 'አ' ጀምሮ በ'ኤ' እንዲያልቅ ሆኖ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ ይህ ቅደም ተከተል ከነባሩ ሀ÷ ለ÷ ሐ÷ መ ሆነ በዕድገት በህብረት ጊዜ ከመጣው በ÷ ሰ÷ ሸ አካሄድ የተለየ ነው፤ የሀ÷ ለ÷ ሐ÷ ቅደም ተከተል ከጥንቱ 'አበገዳ'ዊ ቅደም ተከተል በፍሬምናጦስ ዘመን በግሪኮችና በግብፆች ተፅዕኖ ምክንያት የተለወጠ እንደሆነ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (1948) ፅፈዋል፡፡ ይህ ስነ-ልሳናዊ ሳይሆን ታሪካዊ ምክንያት ነው፡፡

ሁለተኛው መርህ በዕድገት በህብረት ጊዜ ለወጣው 'በ÷ ሰ÷ ሸ'ዊ ቅደም ተከተል መሰረት የሆነው ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደ ተገለፀው በዘመናዊ ትምህርት ቤት ህፃናት ፊደል የሚማሩት እንደ ቄስ ትምህርት ቤቱ እያንዳንድዋን ምልክት በስንጥር እየጠነቆሉ ሳይሆን በወረቀት ላይ እየጻፉ ነው፤ ይህም ምልክትዋን በጥቅል ከማየት መስመራዊ ቅርፅዋን ወደ መለየት ያሸጋግራቸዋል፡፡ ይህ ከሆነ የፊደሎች ቅደም ተከተል ፊደሎቹ በሚወክሉዋቸው ድምፆች የስርጭት ደረጃ ላይ ብቻ ሳይሆን ምልክቶቹ ራሳቸው ለዕይታና ለአጣጣል ባላቸው ገብነት ላይ መመስረት ይኖርበታል፡፡ ይህን ስነ-ዘዴያዊ መርህ ልንለው እንችላለን፡፡ በዚሁ መርህ መሰረት የዚህ ጽሁፍ አዘጋጆች የግል የመማርና የማስተማር ልምዳቸውን÷ እንዲሁም የፊደሎቹን የቅርፅ ውስብስብነት ደረጃ መነሻ በማድረግ የሚከተለውን ቅደም ተከተል አዘጋጅተዋል፡፡

[8] ይህ ስርጭታዊ መጠን ከBender (1974) በመጠኑ ይለያል፡፡

ብ ስ ሽ ል ክ ፕ ት ች ግ ን ኝ ር ፍ

ሀ እ ዕ ው ቅ ዝ ዥ ም ጥ ጭ ይ ድ ጵ

ጅ እ ኣ ኡ ኢ ኦ ኤ እ

ይህ ዝርዝር ቀደም ሲል በተመለከትነው ዝርዝር በቅደም ተከተላዊነቱ ብቻ ሳይሆን በይዘቱም ይለያል። በፊተኛው ዝርዝር ውስጥ የነበሩት እንደ ቈ÷ ኰ÷ ጐ÷ እና ኹ ያሉትን አልያዘም። እነዚህ ተራ ሳይሆን ውስብስብ ምልክቶች ናቸው። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ተራ ሳይሆን ውስብስብ ፎኒሞችን መወከላቸው ነው። ይሁን እንጅ ከአናባቢዎቹ ጋር ሲቀናጁ የሚፈጥሩዋቸው ቅርፆች ከሌሎች ቅንጅቶች ጋር ስለሚመሳሰሉ÷ ካልተመሳሉም በተከታታይ

ተራ ምልክቶች ስለሚወከሉ ከዝርዝሩ ሊወጡ ችለዋል።ውስብስቦቹን ፎኒሞች በውስብስብ ምልክቶች ከመወከል ይልቅ በተከታታይ ተራ ምልክቶች መወከል በተለይ ከትምህርት አቀራረብና ከትየባ ስራ አኩዋያ ሲታይ ጥሩ አማራጭ ነው። ለምሳሌ (ኰ) ከ(ኦ) ጋር ሲቀናጅ የሚፈጥረው ቅርፅ 'ኰ' ነው። በዚህና የ(ክ) እና የ(ኦ) ቅንጅት በሆነው በ'ኮ' መካከል የንበት ልዩነት የለም። የትርጉም ለውጥም አያመጣም። ስለዚህ እነዚህንም ሆነ እንደ ኳ÷ ጓ ወዘተ ያሉትን ኩዋ÷ ጉዋ እያሉ አንዱን ውስብስብ ምልክት ወደ ሁለት ተራ ምልክቶች በመመንዘር መጻፍ ይቻላል። ይህን ካደረግን የፊደሉ ቁጥር ይቀንሳል። በተለይ አዲስ ለሚጻፉ ቁዋንቁዋዎች ይህ ጥሩ አማራጭ ነው።

እንደ ቧ÷ ሏ÷ ሟ÷ ወዘተ ያሉት ምልክቶች በሶስተኛ ደረጃ የሚታዩ የቅንጅት ቅንጅት ናቸው፤ መጀመሪያ ተናባቢው ከ(ኡ) ጋር ይቀናጃል÷ የሁለቱ ውጤት የሆነው ቅንጅት እንደገና ከ(ኣ) ጋር ይቀናጃል። ይህ ሁለተኛው ቅንጅት ውስጥ ያለው (ኣ) እና በመጀመሪያው ቅንጅት ውስጥ ያለው (ቁ) ክትትሎሽ (ኡ)ን ወደ (ው) ይለውጠዋል። እኒህ (ው) እና (ኣ) ደግሞ 'ዋ'ን (ው+ኣ)ን ይፈጥራሉ። ይህም አፃፃፉን 'ሱዋ'÷ 'ኩዋ'÷ 'ሹዋ' ያደርገዋል።

እነዚህን ሁኔታዎች ስናጤን÷ የመጀመሪያው የትምህርት ደረጃ ከላይ የተዘረዘሩት 34 ምልክቶች ብቻ የሚቀርቡበት ይሆናል ማለት ነው። ምልክቶቹ የቁዋንቁዋውን የተለያዩ ፎኒሞች ስለሚወክሉ አብዛኞቹ በቅርፅ የተለያዩ ናቸው። መጠነኛ ተመሳሳይነት የሚታየው የድድ እና የላንቃ ድምፆችን በሚወክሉት እንደ [ሰ÷ሸ]÷ [ደ÷ጀ] ወዘተ. ባሉት መካከል ነው። ተማሪዎቹ እነዚህን 34 ምልክቶች በምድብ በምድብ ከፋፍለው ሊማሩዋቸው ይችላሉ። (አባሪ ሁለትን ይመልከቱ)። በዚህ ደረጃ ያለውን ትምህርት

ሲጠርሱ ፊደል ልዩ ይባላሉ። በዚሁ ዕውቀት ላይ የተመሰረተ ንባብም ይጀምራሉ። ንባቡ ከላይ የተዘረዘሩትን ምልክቶች በመገጣጠም በሚፈጠሩ እንደ:-

ብስ፥ ሽል፥ ስስ፥ ሽሽ፥ ወዘተ

ያሉ ቃላትን የሚያካትት ይሆናል። ቃላቱ ለዐይንም ሆነ ለእጅ ቀላል ስለሆኑ ተማሪዎች በቀላሉ ያነቡዋቸዋል፥ ይጽፉዋቸዋልም። ከዚህ ደረጃ በሁዋላ የሚመጣው ትምህርት የቀለም ነው። ይዘቱም ተናባቢና አናባቢ ፎኒሞችን የሚወክሉ ምልክቶች (ፊደሎች) የሚፈጥሩት ቅንጅት ነው። ይህ ቅንጅት ከሰባቱ የአናባቢ ምልክቶች ስድስቱ ከ27ቱ የተናባቢ ምልክቶች ጋር የሚፈጥሩት ነው። የቅንጅቱ ተዋረዳዊ ቅደም ተከተል ከፍ ሲል እንደተመለከተው በ 'ብ' ጀምሮ በ'ጅ' ይጠርሳል። ወርዳዊ አካሄዱ ደግሞ በስድስቱ አናባቢዎች ስርጭታዊ ደረጃ ላይ የተመሰረተ ይሆናል። የዚህ ፅሁፍ አዘጋጆች ባደረግነው ስርጭታዊ ስሌት የአናባቢዎቹ ቅደም ተከተል የሚከተለው ነው፤

አ ኣ (እ) ኡ ኢ ኦ ኤ

(እ) አትቀናጅም፤ ምክንያቱም እስዋ ሳድስ ፈጣሪ ነበረች። ባሁኑ አካሄዳችን ደግሞ ሳድሶች የተራ ተናባቢ ተራ ምልክቶች እንጅ ቅንጅቶች አይደሉም። ስለዚህ በቅንጅቱ ውስጥ የሚገቡት ሌሎቹ አናባቢዎች ብቻ ናቸው በዚህ መሰረት የቀለሙ ትምህርት ወርዳዊና ተዋረዳዊ አካሄዱ እንደሚከተለው ይሆናል:-


| ፊደል | ቀለም |
|---|---|
| ብ | በ ባ ቡ ቢ ቦ ቤ |
| ስ | ሰ ሳ ሱ ሲ ሶ ሴ ወዘተ. |

ይህ አካሄድ በአናባቢዎቹ የስርጭት ደረጃ ላይ ይመሰረት እንጅ ከስነ-ዘዴ አኩዋያ ሲታይ እንደሚከተለው ሆኖ ቢስተካከል ይበልጥ ስርዓታዊ እንደሚሆን የፅሁፉ አዘጋጆች ያምናሉ።

በ ቡ ቢ ቤ ባ ቦ

ሰ ሱ ሲ ሴ ሳ ሶ (አባሪ ሶስትን ይመልከቱ)

በዚህ አይነት ከግዕዝ እስከ ሳብዕ የሚቀናጁት ምልክቶች መሰረት የእያንዳንዱ ተናባቢ ፎኒም ምልክት (ፊደል) ነው፡፡ ይህ ምልክት አብሮት የሚቀናጀውን የአናባቢ ፎኒም ልዩ ምልክት ይወርሳል፡፡ አቀነጻጀቱ እንደሚከተለው ነው፡፡





'በ' የ[ብ] እና የ[አ] ቅንጅት ነች፡፡ እንደሌሎቹ አናባቢዎች ምልክት የላትም፡፡ ሌጣ ነች፡፡ [ብ] ከዚች ሌጣ አናባቢ ጋር ስትቀናጅ የ[አ]ን ምልክት-የለሽነት ባህሪ ወርሳ እርስዋም ሌጣ 'በ' ትሆናለች፡፡ 'ቡ' የ(ብ) እና የ(ኡ) ቅንጅት ነች፡፡ በመሆንዋም የ(ኡ)ን ልዩ ምልክት ትወስድና ልክ እንደ (ኡ) እስዋም በቀኝ እግርዋ መሀል ጎን ላይ ምልክቱን ትቀጥላለች፡፡ የሌሎችም የአቀናጀጃት ስርዓት ይኸው ነው፤ የየራሳቸውን ልዩ ምልክት እየጣሉ የአናባቢዋን ምልክት መቅዳት (መኮረጅ)፡፡

ከዚህ ላይ የአናባቢዎቹን ምልክት በተመለከተ አንድ ጥያቄ ማንሳት ይቻላል፡፡ ይኸውም ሰባቱ የአናባቢ ምልክቶች የተለያዩ አናባቢ ድምፆችን ይወክሉ እንጅ በቅርፃቸው ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ይህ ተመሳሳይነት ከምን የወጣ ነው? የተመሳሳይነቱን መንስዔ ለመግለፅ፥ ባይመሳሰሉ ምን ሊመስሉ ይችሉ ነበር? የሚል ሌላ ጥያቄ ማንሳት ያስፈልጋል፡፡ በነገሮች መካከል ተመሳሳይነት የሚኖረው አንድም ባጋጣሚ አልያም ነገሮች የጋራ መነሻ ሲኖራቸው ነው፡፡ እያንዳንዱ ነገር የጋራ ሳይሆን የግል ባህሪ ወይም መነሻ (ምንጭ) ካለው ከእያንዳንዱ ሌላ ነገር የተለየ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ ከተናባቢ ፎኒሞች ምልክቶች መካከል የድድና የላንቃ ፎኒሞችን የሚወክሉት እንደ 'ሰ' እና 'ሸ' ያሉት የቅርፅ ተመሳሳይነት የሁለቱም የጋራ መደብ ከሆነው ከ 'በ' ቅርፅ የመጣ ነው፡፡ 'በ' የጋራ መደባቸው ነው ማለት ነው፡፡ በዚህ አይነት ሰባቱን የአናባቢ ምልክቶች ስንመለከት ተመሳሳይም ልዩም ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ተመሳሳይነታቸው ሁሉም 'አ' የሚለውን ምልክት በጋራ መያዛቸው ነው፡፡ በዚህ ምልክት የተለያየ አካል ላይ አንዲት ጭረት (-) ተዘርግታ ወይም ተቆልምማ በመቀጠልም ምልክቶቹን በመነሻቸው አንድ በመድረሻቸው ልዩ ልዩ እንዲሆኑ አድርጋቸዋለች፡፡ በመነሻው፥ ማለትም በመደቡ ቅርፅ ላይ የሰርዝዋ አቀጣጠል እንደሚከተለው ነው፡፡

አ አ-- አ_ አ አ አ አ

ቀደም ሲል እንደ ተመለከተው ተናባቢ ፎኒሞችን የሚወክሉት ምልክቶች ከእነዚህ የአናባቢ ምልክቶች ጋር ሲቀናጁ የየራሳቸውን የግል ምልክት እየጣሉ የየተቀናጁን አናባቢ ልዩ ጭረታዊ ምልክት አናባቢው ምልክት ላይ ባለበት መልኩ ይቀጥላሉ። እንደገና እንመልከተው።




ቀደም ሲል እንደተገለፀው (ብ) ልዩ ምልክት አላት። ይህን ልዩ ምልክትዋን ጥላ የ(ኡ) ጭረት በቀኝ ዕግርዋ መሀል ላይ በመቀጠል 'ቡ' ሆናለች። የሌሎቹም አካሄድ እንደዚሁ ነው። በሌላ አነጋገር የተናባቢዎቹ ምልክቶች የአናባቢዎቹን ምልክቶች እየወሰዱ የቅርፅ ስምምነት ይፈጥራሉ ማለት ነው።

የአናባቢዎቹ ምልክቶች ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው ከአንድ መሰረት ላይ ስለተነሱ ሊመሳሰሉ ችለዋል። የአንድ እናት ልጆች ናቸው ለማለት ይቻላል። ይህ ባይሆን ኖሮ በእንግሊዝኛ እንደሚታየው እያንዳንዱ አናባቢ ከእያንዳንዱ ሌላ አናባቢ ምልክት በቅርፅ የተለየ ይሆን ነበር።

ከላይ በተመለከተው አይነት የተቀናጁትን ምልክቶች እንደ ፊደሉ ትምህርት ደረጃ በደረጃ እያደረጉ ለተማሪው ማቅረብ ይቻላል። በፊደሉ ደረጃ ላይ ፊደሎችን እያገናኙ እንደ:-

ብስ

ስብ

ስስ ወዘተ.

ያሉ ቃላትን ማንበብና መፃፍ እንደሚለማመድ ሁሉ፥ በዚህ በሁለተኛውም ደረጃ እንደ:-

በሳ

ሰባ

ሳሳ

ሳበ ወዘተ.

ያሉ ቅንጅቶችን ማንበብና መፃፍ ይችላል።

ይህ እንግዲህ የስርዓተ-ፅህፈቱ ባለ ሁለት ፈርጅ መሆን በአማርኛው መሰረተ-ትምህርት ላይ የሚኖረውን አንድምታ በተመለከተ ነው። ጉዳዩ ግን በአማርኛ ብቻ የሚወሰን አይደለም። ሌሎች በዚሁ ስርዓተ-ፅህፈት የሚፅፉና መፃፍም የሚፈልጉ ቋንቋዎችንም ሊያዳርስ ይችላል። በዚህ ረገድ የየቋንቋዎቹ የምልክት መጠን በፎኒሞቻቸው መጠን ላይ የተመሰረተ ይሆናል። ለምሳሌ አናባቢዎችን ብንወስድ÷ እንደ አማርኛ ያሉ የሴም ቋንቋዎች ሰባት አናባቢዎች ሲኖሩዋቸው እንደ ኦሮምኛ ያሉ የኩሽ ቋንቋዎች አምስት ብቻ አሉዋቸው። የስርጭት መጠናቸውም ከአማርኛው አናባቢዎች መጠን የተለየ ሊሆን ይችላል። ስለዚህም የተናጠላዊውም (ፊደላዊ) ሆነ የቅንጅታዊው ወርዳዊና ተዋረዳዊ ዝርዝር እንደየቋንቋዋው የተለያየ ሊሆን ይችላል።

ቀደም ሲል የጠቀስነውን የቀቤናን ዝርዝር ብንመለከት የቅንጅቱ አካሄድ እንደሚከተለው ነው።

ቡ ቢ ቤ ባ ቦ

የቋንቋዋው አናባቢዎች አምስት ስለሆኑ ወርዳዊ ዝርዝሩ በአምስት ብቻ ሊወሰን ችሉአል። እነዚህ በአጭር አናባቢ የተፈጠሩ ቅንጅቶች ናቸው። ቋንቋዋው ደግሞ ባለ አጭር ብቻ ሳይሆን ባለ ረዥም አናባቢም ነው። ስለዚህም እያንዳንዱ ተናባቢ ከረዥም አናባቢ ጋር ሲቀናጅ ዝርዝሩ የሚከተለውን ይመስላል፡-

ቡኡ ቢኢ ቤኤ ባአ ቦኦ

በዚሁ መሰረት ረዥም አናባቢ ያላቸው የቀቤና ቃላት እንደሚከተለው ይፃፋሉ፡-

ባአዱ 'ሀገር'

'ባ' በሚለው ቅንጅት ውስጥ አንድ (አ) አለ በዚህ ቅንጅት ላይ ሌላ (አ) በመጨመር አናባቢው ረዥም መሆኑን ማመልከት ይቻላል። የተናባቢ ጥብቀትንም እንደዚሁ ተጨማሪ ምልክት በመጠቀም ማሳየት ይቻላል። እሁንም የሚከተለውን የቀቤና ምሳሌ እንመልከት፡-

መንና 'ሰዎች'

በዚህ ቃል ውስጥ (ን) ጥብቅ ነው። ይህንን ጥብቀት 'ና' ከሚለው ቅንጅታዊ ምልክት በፊት ተጨማሪ (ን) በማስገባት ማሳየት ይቻላል። ሁኔታው ቀደም ሲል እንዳየነው 'ገንና' እንደሚለው የአማርኛ ቃል አፃፃፍ ነው።

## 4. ማጠቃለያ

በዚህ ፅሁፍ ይዘነው የተነሳነው አቢይ ጉዳይ የምንጠቀምበት ስርዓተ-ፅህፈት ምናዊነት ነበር። ታደሰ (1994) ቀለማዊ አይደለም ካለበት ተነስተን ቀለማዊ ያልሆነበትን ምክንያት ከሌሎች ስርዓተ-ፅህፈቶች ጋር በማነፃፀር ብቻ ሳይሆን ስርዓተ-ፅህፈቱ የሚጠቀምባቸውን ምልክቶች በመመርመር ስርዓቱ ፊደላዊ እንደሆነ አሳይተናል። ይሁን እንጅ እንደ ሌሎች ፊደላዊ ስርዓተ-ፅህፈቶች እያንዳንዱን ፎኒም በተራ (ፊደል) ብቻ ሳይሆን የተናባቢና የአናባቢ ፎኒሞችን ምልክቶች እያቀናጀ በቅንጅታዊ ምልክት ሁለት ወይም ሶስት ድምፆች እንደሚወክል አይተናል።

ስርዓተ-ፅህፈቱ ፊደላዊ ከሆነ የዚህ አንድምታ ምን ሊሆን ይችላል የሚል ጥያቄ አንስተን ሁለት ጉዳዮችን በዝርዝር ተመልክተናል። የመጀመሪያው የፊደሉ ትምህርት ሲሆን ሁለተኛው ስርዓተ-አፃፃፉ ነው። ስርዓተ-አፃፃፉ ተናጠላዊ እና ቅንጅታዊ ከሆነ ትምህርቱም የፊደልና የቀለም ተብሎ በሁለት፥ ምናልባትም በሶስት መመደብ እንዳለበት አይተናል። በፊደል ደረጃ የሚቀርበው ትምህርት እስከ ዛሬ ድርስ ሳድስ ተብለው የሚጠሩትንና ሰባቱን የአናባቢ ምልክቶች የሚያካትት ይሆናል። የእነዚህም አቀራረብ በሚወክሉዋቸው ድምፆች ስርጭታዊና እጅ-ገባዊ ደረጃ መወሰን እንዳለበት ገልጸናል።

በቀለም ደረጃ የተናባቢዎቹና የአናባቢዎች ምልክቶቹ ሲቀናጁ የሚፈጥሩዋቸው ቅንጅታዊ ምልክቶች የሚቀርቡበት ነው። ቅንጅቶቹ ባለ ሁለት ረድፍ ሊሆኑ እንደሚችሉም አይተናል። የመጀመሪያው ረድፍ አንድ ተናባቢና አንድ አናባቢ ብቻ የሚቀናጁበት ነው። በዚሁ መሰረት በቀለም ደረጃ የሚቀርበው ትምህርት በሁለት ተከፍሎ በቅደም ተከተል መቅረብ እንደሚኖርበት አይተናል።

ሁለተኛው አንድምታ በራሱ በስርዓተ-አፃፃፉ ላይ ነው። በማንኛውም ፊደላዊ ስርዓተ-ፅህፈት እንደሚደረገው እያንዳንዱን ድምፅ በተናጠል ምልክት ብቻ ማመልከት ይቻላል። እንደዚህ እያደረጉ መፃፍ የድምፆችን የመጥበቅና የመላላት፥ የመርዘምና የማጠር፥ ወዘተ ባህርያት ማመልከት ስለሚቻል ይህን ባለማመልከት ሊመጣ የሚችለውን የአሻሚነትና የአነባበብ ችግር ማስወገድ ይቻላል። ይሁን እንጅ የማንኛውም ሰው የቀዋንቁዋ ዕውቀት የድምፆችን ልዩ ልዩ ባህሪያት ስለማያጠቃልል እያንዳንዱን ድምፅ ከነልዩ

ባህሪው ማመልከት አስቸጋሪ ይሆናል። አስቸጋሪነቱ የአፃፃፍ (ሆሄ) ነው። አንዱ የሚያጠብቀውን ሌላው ስለሚያላላው ትምህርቱ የፊደል ብቻ ሳይሆን የሆሄም ይሆናል። ለዚህ ችግር እንደ መፍትሄ የወሰድነው የትርጉም አሻሚነት የሚያስከትሉትን ድምፆች ብቻ በተናጠል እያመለከቱ ሌሎቹን አማርኛ እንደሚያደርገው በቅንጅት ማመልከት ነው። በዚህ አካሄድ የሆሄውን ችግር ደረጃ በመጠኑ መቀነስ ይቻላል።' በዚሁ ዐይነት ስርዓተ-ዕህፈቱን ማሻሻል ለማንኛውም የሀገራችን ቁዋንቁዋ መፃፊያ ሊሆን እንደሚችል በቀቤና ላይ የተደረገውን ጥናት በአብነት ጠቅሰናል።

አባሪ አንድ: የስርጭት ደረጃ

| ፊ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | ድ | አ | ደ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ም | 172 | 243 | 139 | 172 | 142 | 159 | 170 | 1197 | 171 | 1 |
| ት | 135 | 210 | 240 | 157 | 91 | 171 | 178 | 1182 | 168.9 | 2 |
| ን | 137 | 183 | 216 | 185 | 109 | 171 | 167 | 1168 | 166.9 | 3 |
| ል | 133 | 169 | 182 | 102 | 112 | 132 | 185 | 1015 | 145 | 4 |
| ብ | 113 | 152 | 165 | 178 | 51 | 138 | 163 | 960 | 137.14 | 5 |
| ር | 170 | 146 | 159 | 124 | 66 | 121 | 13 | 889 | 127 | 6 |
| ይ | 104 | 134 | 181 | 36 | 112 | 129 | 155 | 851 | 121.6 | 7 |
| ው | 78 | 111 | 114 | 95 | 62 | 82 | 49 | 591 | 84.4 | 8 |
| ስ | 81 | 76 | 148 | 90 | 50 | 96 | 49 | 590 | 84.3 | 9 |
| ግ | 75 | 95 | 96 | 82 | 33 | 35 | 79 | 542 | 77.4 | 10 |
| ድ | 83 | 104 | 86 | 70 | 48 | 46 | 62 | 488 | 69.7 | 11 |
| ክ | 40 | 100 | 52 | 38 | 39 | 87 | 99 | 414 | 59.1 | 12 |
| ች | 39 | 69 | 70 | 34 | 87 | 33 | 38 | 395 | 56.4 | 13 |
| ጥ | 43 | 68 | 75 | 40 | 31 | 35 | 58 | 348 | 49.7 | 14 |
| ቅ | 38 | 54 | 72 | 59 | 35 | 15 | 43 | 336 | 48 | 15 |
| ህ | 57 | 48 | 88 | 36 | 47 | 42 | 40 | 331 | 47.3 | 16 |
| ፍ | 32 | 43 | 24 | 17 | 26 | 43 | 51 | 235 | 33.6 | 17 |
| ? | 26 | 28 | 34 | 23 | 14 | 3 | 3 | 171 | 24.4 | 18 |
| ጅ | 9 | 25 | 14 | 12 | 11 | 2 | 16 | 90 | 12.9 | 19 |
| ኝ | 6 | 25 | 13 | 11 | 5 | 5 | 14 | 76 | 10.9 | 20 |
| ሽ | 13 | 13 | 3 | 8 | 9 | 8 | 14 | 65 | 9.3 | 21 |
| ፅ | 6 | 16 | 15 | 12 | - | 7 | 1 | 58 | 8.3 | 22 |
| ጭ | 5 | 16 | 4 | 1 | 5 | 2 | 17 | 55 | 7.9 | 23 |
| ዕ | 1 | 4 | 7 | - | 13 | 2 | - | 27 | 3.9 | 24 |
| ፐ | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | - | 6 | 17 | 2.4 | 25 |
| ኅ | - | - | 1 | - | 1 | - | 5 | 7 | 1 | 26 |
| ቀ | 1 | - | 2 | - | - | - | 1 | 4 | 0.57 | 27 |
| ኸ | 1 | - | 2 | - | - | - | 1 | 4 | 0.57 | 27 |
| ከ | - | - | - | - | - | - | 4 | 4 | 0.57 | 27 |
| ዣ | 2 | - | - | - | - | - | 2 | 2 | 0.57 | 27 |
| ጽ | 2 | - | - | - | - | - | 1 | 3 | 0.43 | 38 |
| አ | 471 | 675 | 678 | 451 | 198 | 445 | 460 | 3378 | 482.6 | 1 |
| ኣ | 349 | 451 | 458 | 163 | 128 | 273 | 388 | 2160 | 308.6 | 2 |
| እ | 173 | 265 | 262 | 219 | 128 | 116 | 180 | 1343 | 191.9 | 3 |
| ኡ | 69 | 101 | 118 | 44 | 36 | 77 | 55 | 500 | 71.43 | 4 |
| ኢ | 61 | 67 | 114 | 48 | 28 | 92 | 68 | 478 | 68.29 | 5 |
| ኦ | 77 | 60 | 103 | 38 | 30 | 72 | 65 | 445 | 63.57 | 6 |
| ኤ | 23 | 22 | 48 | 71 | 10 | 19 | 25 | 218 | 31.14 | 7 |

## አባሪ ሁለት የፊደል ትምህርት ደረጃ

ትምህርት አንድ፣

| ፊደል | ንባብ መልመጃ |
|---|---|
| ብ | ብስ |
| ስ | ሽሽ |
| ሽ | ስብ |

ትምህርት ሁለት፣

| | |
|---|---|
| ት | ትት |
| ች | |

ትምህርት ሶስት፣

| | |
|---|---|
| ፐ | ግን |
| ን | ግግ |
| ኝ | |
| ግ | |

ትምህርት አራት፣

| | |
|---|---|
| ህ | ዕዕ |
| ዕ | ዕህ |
| ዕ | |

ትምህርት አምስት፣

| | |
|---|---|
| ው | ውቅ ቅን |
| ቅ | ቅዕ ቅኝ |

ትምህርት ስድስት፣

| ፊደል | ንባብ መልመጃ |
|---|---|
| ዝ | ዕዝ |
| ዥ | ዕዥ |

ትምህርት ሰባት፣

| | |
|---|---|
| ም | ምጥ |
| ጥ | ጥም |
| ጭ | ውጭ |

ትምህርት ስምንት፣

| | |
|---|---|
| ይ | ድድ ድጥ |
| ድ | ዕይ |
| ? | ዕጅ |
| ጅ | ጅብ |
| ጵ | ድብ |

ትምህርት ዘጠኝ፣

| | |
|---|---|
| ል | ልል ድል ውል |
| ክ | ልክ ጅል ውድ |

ትምህርት አስር፣

| | |
|---|---|
| ፍ | ግፍ ፍግ ንክ |
| ር | ክር ድር ስር |

### ትምህርት አስራ አንድ፣

እ፥ አ፥ ኣ፥ ኡ፥ ኤ፥ ኢ፥ ኦ

## አባሪ ሶስት የቀለም ገበታ

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| በ(አ) | ብ(ኡ) | ቢ(ኢ) | ቤ(ኤ) | ባ(ኣ) | ቦ(ኦ) | |
| ሰ(አ) | ሱ(ኡ) | ሲ(ኢ) | ሴ(ኤ) | ሳ(ኣ) | ሶ(ኦ) | |
| ሸ(አ) | ሹ(ኡ) | ሺ(ኢ) | ሼ(ኤ) | ሻ(ኣ) | ሾ(ኦ) | |
| ለ(አ) | ሉ(ኡ) | ሊ(ኢ) | ሌ(ኤ) | ላ(ኣ) | ሎ(ኦ) | |
| ከ(አ) | ኩ(ኡ) | ኪ(ኢ) | ኬ(ኤ) | ካ(ኣ) | ኮ(ኦ) | |
| ፐ(አ) | ፑ(ኡ) | ፒ(ኢ) | ፔ(ኤ) | ፓ(ኣ) | ፖ(ኦ) | ፒ(?) |
| ተ(አ) | ቱ(ኡ) | ቲ(ኢ) | ቴ(ኤ) | ታ(ኣ) | ቶ(ኦ) | ቲ(?) |
| ቸ(አ) | ቹ(ኡ) | ቺ(ኢ) | ቼ(ኤ) | ቻ(ኣ) | ቾ(ኦ) | ቺ(?) |
| ገ(አ) | ጉ(ኡ) | ጊ(ኢ | ጌ(ኤ) | ጋ(ኣ) | ጎ(ኦ) | |
| ነ(አ) | ኑ(ኡ) | ኒ(ኢ) | ኔ(ኤ) | ና(ኣ) | ኖ(ኦ) | |
| ኘ(አ) | ኙ(ኡ) | ኚ(ኢ) | ኜ(ኤ) | ኛ(ኣ) | ኞ(ኦ) | |
| ረ(አ) | ሩ(ኡ) | ሪ(ኢ) | ሬ(ኤ) | ራ(ኣ) | ሮ(ኦ) | |
| ፈ(አ) | ፉ(ኡ) | ፊ(ኢ) | ፌ(ኤ) | ፋ(ኣ) | ሆ(ኦ) | |
| ሀ(አ) | ሁ(ኡ) | ሂ(ኢ) | ሄ(ኤ) | ሃ(ኣ) | ሆ(ኦ) | |
| ዐ(አ) | ዑ(ኡ) | ዒ/ዒ(ኢ) | ዔ/ዔ(ኤ) | ዓ/ዓ(ኣ) | ዖ(ኦ) | |
| ፀ(አ) | ፁ(ኡ) | ፂ(ኢ) | ፄ(ኤ) | ፃ(ኣ) | ፆ(ኦ) | |
| ወ(አ) | ው(ኡ) | ዊ(ኢ) | ዌ(ኤ) | ዋ(ኣ) | ዎ(ኦ) | |
| ቀ(አ) | ቁ(ኡ) | ቂ(ኢ) | ቄ(ኤ) | ቃ(ኣ) | ቆ(ኦ) | |
| ዘ(አ) | ዙ(ኡ) | ዚ(ኢ) | ዜ(ኤ) | ዛ(ኣ) | ዞ(ኦ) | |
| ኸ(አ) | ኹ(ኡ) | ኺ(ኢ) | ኼ(ኤ) | ኻ(ኣ) | ኾ(ኦ) | |
| መ(አ) | ሙ(ኡ) | ሚ(ኢ) | ሜ(ኤ) | ማ(ኣ) | ሞ(ኦ) | |
| ጠ(አ) | ጡ(ኡ) | ጢ(ኢ) | ጤ(ኤ) | ጣ(ኣ) | ጦ(ኦ) | |
| ጨ(አ) | ጩ(ኡ) | ጪ(ኢ) | ጬ(ኤ) | ጫ(ኣ) | ጮ(ኦ) | |
| የ(አ) | ዩ(ኡ) | ዪ (ኢ) | ዬ(ኤ) | ያ(ኣ) | ዮ(ኦ) | |
| ደ(አ) | ዱ(ኡ) | ዲ(ኢ) | ዴ(ኤ) | ዳ(ኣ) | ዶ(ኦ) | |
| ጸ(አ) | ጹ(ኡ) | ጺ(ኢ) | ጼ(ኤ) | ጻ(ኣ) | ጾ(ኦ) | |
| ጰ(አ) | ጱ(ኡ) | ጲ(ኢ) | ጴ(ኤ) | ጳ(ኣ) | ጶ(ኦ) | |
| ጀ(አ) | ጁ(ኡ) | ጂ(ኢ) | ጄ(ኤ) | ጃ(ኣ) | ጆ(ኦ) | |

*'ሀ' የሚለው ቅንጅታዊ ምልክት የሚወክለው በተለመደው አጻጻፍ 'ኸ' የሚለው ምልክት የሚወክለውን ቅንጅት ነው:: በዚህ ጥናት መሰረት 'ኸ' መኖረ አይገባውም:: እሱ የሚወክለው ቅንጅት በ'ሀ' ይወከላል:: 'ሀ' ይወክለው የነበረው ደግሞ በራብዑ 'ሃ' ይወከላል:: የ'ሀ' እና የ'ዓ' ውክልናም እንደዚሁ ነው:: ስለዚህም ሀይሉ የሚለው ሃይሉ+ ዐመል ደግሞ ዓመል ተብሎ በራብዑ ይፃፋል::